ጊዜው በኢትዮጵያ አቆጣጠር 1969 ኢ.ም. በየካቲት ወር ነው፤ ከስራ እና ከመኖሪያ ቤታችን ከወጣን ስድስት ወር አልፎናል፤፤ ኑሮአችን ቀን በየሻይና ቡና ቤት፤ ማታ ደግሞ ከደርግ ጋር ምንም ንክኪ የሌላቸው፤ ምሲጥር የሚጠ-በቁ ዘመዶች ፣ ጉዋዶች ጋር  እሱም ከጠፋ በየተገኘበት እናድራለን፤፤ የአሰሳውም ሁኔታ በጣም እየጠበቀ ስለመጣ የተሸሎክልኮ ኑሮ እየጠበበ፣ በደርግ ተይዞ የመታሰር ወይም የመገደል እድላችን በጣም እየሰፋ መጥቶ ተስፋ ወደ መቁረጡ አዝማማያ እያለን አንድ ጉዋድ የምስራች ይዞልን መጣ፣፣ በእነ አለማየሁ፤ ሞገስ፣ ተፈሪ በንቲ የተካሄደው መፈንቅለ መን ግሰት ስለከሸፈ መንግሰቱ እና ግ-በረ አበሮቹ የአዲሰ አበባን ከተማ ዘግተው ጠቅላላ አሰሳ ለማካሄድ ትልቅ ዝግጁት እየተደረገ ስለሆነ እናንተ ወደ አሲምባ እንድተወጡ አስፈላገው ነገሮች ሁሉ እየተዘጋጀላችሁ ነው -በሎ ሲነግረን ፈነደቅን፤፤

እኔ እሰራበት ከነበረው መስሪያ ቤት -በዙ ሰዎች ከስራቸው የተባረሩም ቢኖሩም በቅር-ብ የምንገናኘው ከአስር አንበልጥም ነበር፤፤ ጥቂቶች እራሳቸውን አግለው በግላቸው ሲዋትቱ ሌሎች ደግሞ ተስፋ በመቁረጥ ለደርግ እጃቸውን የሰጡ ነበሩ፤፤ እኛ ግን የህንን ተስፋ አግኝተን ዝግጁታችንን ጀምርን ፤፤ አስፈላጊ ናቸው ከተባልነው መሀከል ሰአት፣ ሬድዮ፣ ጂንስ ሱሪ፤ እና የተቻለውን ያህል ገንዘ-ብ መሰ-በሰ-ብ ጀመርን፤፤ ታናሽ ወንድሜን ፤በሁዋላ በቀይ ሽ-በር ተሰውቶአል ፤ ከአባቴ ገንዘ-ብ የ እህቴን ጂንስ እንዲያመጣልኝ ልኬው በሁለተኛው ቀን ሁሉንም አዘጋጁቶ ይዞ መጣልኝ፤፤ ሁላችንም በዚህ አይነት መዘጋጃጀት ጀመርን፤፤ የህንን በምናደርግበት ጊዜ ሁላችንም ከደስታችን -በዛት ደርግ መኖሩንም የዘነጋነው ይመስል ነበር፤፤

የመሄጃችንም ቀን እንደማይደርስ የለምና ደረሶ እኔና ሰለሞን ተፈሪ (ደምስ) አንድ ላይ አድረን ጥዋት የጠቅላይ ግዛት መኪና ተራ ሁላችንም 7 ሀጂዎች ተገናኘን፤፤ እዛም ከድርጁቱ ተወክሎ የመጣው ጉዋድ የመታወቂያ ወረቀቶችን እና ሌሎችም አስፈላጊ ነገሮችን የዞልን መጣ፤፤ ከዛ ጊዜው ደርሶ እዛ ከሚቀረው ጉዋድ ጋር ተሰነባ-በተን ኦቶ-በሳችን ላይ ተሳፈርን፤፤

በዚህ ጉዞ አንድ ላይ ከተሳፈርነው አራታችን ከአንድ መስሪያ ቤት ነበርን፤፤ አሁን በይህወት የአለሁት እኔ -ብቻ ነኝ፤፤ ሌሎቹ 3 ጉዋዶች አንድ ከባንክ፤ አንድ ከሂልተን፣ አንዱን ገዋድ ከየት መስሪያ ቤት አንደሆነ አሁን አላስታውስም፤፤ ሁላችንም ተሰበጣጥረን ኦቶቡሱ ላይ ተቀመጥ ጉዞአችንን ወደ ትግራይ ጀመርን፤፤ ከሶስት አራት የጭንቀት ፍተሻ በሁዋላ ደሴ ወደ 11 ሰአት ከቀኑ ምሽት አካባቢ ደረስን፤፤ ፍተሻው ያስጨነቀን ምክንያት ከ ሰባታችን ውስጥ ሶስታችን አንድ አይነት መታወቂያ ነበር የያዝነው፤፤ በዚያም ምክንያት አሁን አሁን አስወረዱን ስንል -በዙም ሳይነቁ-በን ደሴ መድረሳችንን እነደ ትልቅ ድል ቆጥረነው ወደ እደሩበት ወደ ተባለው ሆቴል ሄደን አልቤርጎ ያዝን፤፤ ከዚያም በተሰጠን መመሪያ መሰረት አንደኛው ጉዋድ ተገናኝ ወደ ተባለበት ቦታ ሄዶ ካንድ ጉዋድ ጋር ተገናኝቶ አስደንጋጭ ዜና ይዞልን መጣ፤፤ ዜናው የወሎ ክፍለ ሃገር አስተዳዳሪ ከዛ ቀን በፊት በኢህአፓ መገደሉንና የዛን እለት ማታ ትልቅ አሰሳ ስለሚደረግ እንድንጠነቀቅ ነው፤፤ ይህንን ወሬ እንደሰማን ሁለት ሁለት እየሆንን እራታችንን ከበላን በሁዋላ ከአልቤርጎአችን ሳንወጣ የጨንቀት ምሽት አመሸን፤፤ ከዚያም አሁን መጡ አሁን መጡ ስንል ሌሊቱን ሳንተኛ ነጋ፤፤ ጥዋት ስንጠይቅ አገሩን ሲያተራምሱት እኛ የአደርንበትን ሆቴል ግን ዘለውት ሄዱ፤፤ ይቺ ስራ ያናርኪስት ስራ ነች -በለን እግዚአ-በሄርን አመስግነን አሁን ደግሞ ደሴን ለመለቀቅ ቸኮልን፤፤ ሆቴላችን ከኦቶ-በሱ ተራ ቅር-ብ ስለሆነ የረባም ቁርስ ሰንበላ ቦርሳችንን አንጠልጥለን ሄድን፤፤ ኦቶ-በሱ ውስጥ ገ-በተን ጉዞ ልንጀምር ስንል አንድ የማውቀው  የፖስጣ ቤት ሰራተኛ በጣም በደርግ የሚፈለግ ጋር አይን ለአይን ግጥም አልን፤፤ ሰላም እነዳልለው የማጋልጠው መሰለኝ እሱም ሰላም እንዳየለኝ የሚያጋልጠኝ መስሎት ሳይሆን አይቀርም በአይን -ብቻ ማየት እስከቻልን ድረስ ተያይተን ተለያየን፤፤ ልጁ ተይዞ -በዙ ስቃይ ደርሶበት እነደነበር ሰምቻለሁ፤ ይሙት ይዳን አላወቅሁም፤፤

ከ 7 ወይም 8 ሰአት ጉዞ እና ከሶስት አራት ፍተሻ በሁዋላ መቀሌ በጊዜ ገባን፤፤ እዚያም እን ደገባን ሆቴላችንን ከያዝን በሁዋላ ከመሀላችን ገንኙነት የሚፈጥረው ጉዋድ የተባለው ቦታ ሄዶ የመገናኘው ጉዋድ ጠፋ፤፤ ደጋግሞ ቢሞክር አልተሰካም፤፤ ከዚያም ለኛ መጥቶ ሲነግረን፤ ትንሽ ተደናገጥን ግን የደሴውን እሩ-ብ እንኩዋን አይሆንም፤፤ትንሽ ከተወያየን በሁዋላ በየቡና ቤቱ እና በየጠጁ ቤት  መዝናናት ጀመርን፤፤ በመጠጥም ይሁን ተስፋ በመቁረጥ ሁሉም መናዘዝ ጀመረ፤፤ መጀመሪያ ገ-በረ ዮሃንስ አይችሉህም (ፈይሳ) (አሁን ተሰውቶአል) አዲስ አበባ ጥሎአት የመጣውን ለትኩስ ፍቅረኛው ” እኔ ከተሰዋሁ ለጉዋደኛዬ እንደምወዳት ንገሩልኝ “ —በሎ ሀሳ-ብ ውስጥ ተዋጠ፤፤ ከዛም ሰሎሞን ተፈሪም (ደምሰው ) (አሁን በህይወት የለም) የገ-በረ ዮሃኒስን አይነት እሱም ለጉዋደኝው ፍቅሩን እንዲገለጽለት ጠየቀ፤፤ ጌታቸው ከበደም (የሜዳ ስሙ ጠፋኝ) (ተሰውቶአል) ቃል በቃል ባለስታውስም ያንኑ የመሰለ መልእክት አስተላለፈ፤፤ ሁለችንም በተራ በተራ እየተነሳን ተናዘዝን ፤፤ ከአንድ መስሪያ ቤት በአንድ ላይ ከወጣነው አሁን እኔ -ብቻ ስለተረፍኩ የሁሉም ኑዛዜ በእኔ ተከሻ ሌአየጨ ነው ያረፈው፤፤ መልእከቱን በአካል ሄጄ ባደርስ ደስ ባለኝ ነበር ፤፤ ግን አድራሻና ስም ስለሌለኝ በዜህ ጽሁፍ አማካይነት ይድረሳችሁ፤፤

**ሁለተኛው ክፍል ይቀጥላል ,,,,,,**